EthioLion

# የተወዳጁና የተከበረው የአርቲስት ዶክተር ጥላሁን ገሠሠን ከዚህ ዓለም በሞት መለየት አስመልክቶ በቶሮንቶ የተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን አስተባባሪ ኮሚቴ ጥልቅ ሀዘኑን ይገልጻል

ዝነኛውና ታዋቂው የመድረኩ ንጉሥ አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ አገሩንና የኢትዮጵያ ሕዝብን የሚወደውንና የሚያፈቅረውን ያህል የኢትዮጵያ ሕዝብም እጅግ ይወደዋል፣ ያከብረዋል፣ ያፈቅረዋል። አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ልዩ የሆነ የእግዚአብሔር ስጦታውን ተጠቅሞ ሕዝቡንና አገሩን ሲያገለግል፣ ሲያስደስት፣ ሲያስተምር፣ ሲያፋቅር፣ ለአገሩ እንዲዋደቅ ሲቀሰቅስ ማህበራዊ ኑሮውን ሲዳስስ፣ ሲያዝናና የማይጠገበው ዜማው በእያንዳንዱ ኢትየጵያዊ ልብ ውስጥ ጥሎት ያለፈው ልዩ ስሜት የማያረጅና የማይሞት በመሆኑ እየተጽናና፤ ሞት የተፈጥሮ ሕግ ግዴታ ነውና ውዱን የኢትዮጵያ ልጅ በክብርና በፍቅር ወደ ዘላለም መኖሪያው ለመሸኘት ተገዷል።

አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ የማይጠገበውና የማይሰለቸው ድምጹ "የኢትዮጵያ የሙዚቃ ንጉሥ" የሚለውን አርዕስት እንዳሰጠው ይታወሳል። ለረጂም ዘመን በሙያው ላበረከተው አስተዋፅኦም የክብር ዶክትሬት ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲም ተሰጥቶታል። አንጋፋው አርቲስ ጥላሁን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚኖረውን ህይወቱን፤ ባሕሉን፤ እምነቱን፤ ወኔውን፤ ክብሩን፤ ጀግንነቱን፣ ፍቅሩን በጣዕመ ዜማው እያቀነባበረ በመጫወቱ ከልጅነት እስከ አዛውንት እድሜ ክልል ወንድ ሴት ሳይል ሲያስደስት በመኖሩ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቹ በፍቅርና በስስት የሚያዩት ዛሬ ህይወቱ ማለፉን ሲሰሙ በከፍተኛ ድንጋጤና ሀዘን ስሜታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ። አርቲስት ዶክተር ጥላሁን ገሠሠ የሕዝብ ፍቅር ከማግኘት በላይ የሚያስደስተው ነገር እንደሌለም ሲናገር ነበር፣ ይኸው ዛሬ ሕዝቡ ፍቅሩን ሲገልጽለት አየነው።

የአርቲስት ጥላሁን ገሠሠን ፋና ተከትለው የተጓዙም አያሌ ኢትዮጵያውያን አርቲስቶች በህይወት የሌሉትንም በዚሁ አጋጣሚ በክብር እያሰብናቸው፤ በህይወት ያሉትንም በጤና ይጠብቅልን እያልን፤ ለሕዝቡ ፍቅር ሰላምና አንድነት ሲል በማይጠገበው ድምጹ ጣዕመ ዜማውን ሲያሰማን የነበረው አርቲስት ቲዎድሮስ ካሣሁንን /ቴዲ አፍሮን/ እናስበዋለን። ዛሬ የሕዝብ ፍቅር ተቋዳሽ ለመመስል፣ የሕዝቡን ስሜት የሚጋራ ለመምሰል ወያኔ በአንጋፋው አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ ቀብር ላይ ተዋናይ ቢመስልም የሕዝብን ልጅ ቴዲ አፍሮን በሀሰት ክስ በእስር ማሰቃየቱን ስንመለከት ደግሞ እንዳንዘናጋና የወያኔን ማንነት እንዳንረሳ ያደርገናል።

**ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ የተወዳጁን የአርቲስት ዶክተር ጥላሁን ገሠሠን በሞት መለየት የተሰማውን ጥልቅ ሀዘን እየገለጸ፤ ለቤተሰቦቹና ለኢትዮጵያ ሕዝብ መጽናናትን ይመኛል።**

**ተቆርቋሪ ኢትዮጵያውያን በቶሮንቶ**
ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓም
ቶሮንቶ፤ ካናዳ

EthioLion.Com

Ethiopia will prevail !